ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም**፦ ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶሰት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.

# ዜና ዘገባ

**ሐምሌ 17 ቀን 2002 ዓ.ም.**

**ዜጎች እየታፈሱ የሚደርሱበት እየጠፋ መሆኑ ተጠቆመ፤**

**እጃቸውን በካቲና አስረው ያመጡዋቸው እስረኞች በአሰቃቂ ሁኔታ ሞቱ፤**

**የወያኔው መሪ መለስ ባለሀብት ኢትዮጵያውያኖችን አስፈራራ ዛቻም ሰነዘረባቸው፤**

**ለዲፕሎማቶች ታጎበድዳላችሁ ሲልም ወረፋቸው፤**

የወያኔ አረመኔ ቡድን ይቃወሙኛል የሚላቸውን ዜጎች ያለ አንዳች በቂ ማስረጃ በየእስር ቤቱ እያጎረ ከማሰቃየቱም በተጨማሪ ቤተሰቦቻቸው እስረኞቹ ያሉበትን እንዳያውቁ እየደበቀ መሆኑን ከተለያዩ እስር ቤቶች የሚደርሰን ጥቆማ ገለፀ::

በተለይ ከአዲስ አበባ እና ከዋና ዋና የክልል ከተሞች በተለያዩ ሰበቦች እና በተለያዩ ምክንያቶች እየለቀሙ የሚያስሩዋቸውን የፖለቲካ እስረኞች ከቤተሰቦቻቸው ጋር እንዳይገናኙ በማድረግ እያሰቃዩዋቸው ሲሆን ቤተሰቦቻቸው ያሉበትን እስር ቤት ድንገት ቢያውቁ እንኳዋን እንደማያገናኙዋቸው ከጥቆማው ለመረዳት ተችሎዋል::

አደገኛ ቦዘኔ ብለው የወያኔ ባለስልጣናት ስያሜ ያወጡላቸው ወጣቶች በሸዋ ሮቢት እና ሙሰኛ ብለው የሚጠሩዋቸው ነጋዴዎች በዝዋይ እስር ቤቶች ውስጥ ተከፋፍለው እየታሰሩ ሲሆን በእነዚህ ዜጎች ላይ በየእለቱ የሚያደርሱት ግፍ እና በደል በቃላት ሊገለጽ እንደማይችል የተገለፀ ሲሆን እስረኞቹ በሚወሰድባቸው አረመኔያዊ እርምጃ እየተማረሩ እራሳቸውን እስከ ማጥፋት መድረሳቸውን የጠቆሙት ምንጮቹ ሰሞኑን ደግሞ እጆቻቸው በካቴና ታስረው ለህክምና ከዝዋይ ወደ አዲስ አበባ ሲጉዋዙ የነበሩት እስረኞች ላይ የሞት እና ከባድ አደጋ እንደ ደረሰባቸው ታውቆዋል::

ከዝዋይ እስር ቤት ለህክምና ብለው ወደ አዲስ አበባ ሆስፒታል የወሰዱዋቸው እስረኞች ላይ ሞት እና የመቁሰል አደጋ የደረሰው ቅጥ ያጣ የአነዳድ ችግር ከመሆኑም በተጨማሪ እስረኞቹ ከመኪናው መቀመጫ እጀታ ጋር ሁለት እጆቻቸው በመታሰሩ መኪናው ሲገለበጥ የከፋ አደጋ ሊደርስባቸው እንደቻለ ከአይን እማኞች የተገኘው ጥቆማ አስረድቶዋል::

እጃቸውን በካቴና ታስረው ከዝዋይ ወደ አዲስ አበባ ሲወሰዱ የነበሩት እስረኞች ከዝዋይ 50 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ዓለም ገና ተብላ በምትጠራው ከተማ አቅራቢያ ሲደርሱ ከሌሊቱ 10 ሠዓት ላይ የመኪና መገልበጥ አደጋ እንደደረሰና ሁለት እስረኞች ወዲያውኑ ሲሞቱ ሌሎች ደግሞ እጅግ የከፋ አደጋ እንደደረሰባቸው ለማወቅ ተችሎዋል::

ሀምሳ አለቃ ዮሀንስ በተባለ አሽከርካሪ እሁድ ሐምሌ 11 ቀን 2002 ዓ.ም ለሰኞ አጥቢያ ከሌሊቱ 10 ሰዓት ላይ ከዝዋይ እስር ቤት ወደ አዲስ አበባ እስረኞችን ይዞ ሲበርር የነበረ ኮስተር የተሰኘ 24 ሰው የሚጭን መለስተኛ አውቶቡስ ተገልብጦ ሁለት እስረኞች ወዲያውኑ ሲሞቱ ሌሎች ከባድ የመቁሰል አደጋ የደረሰባቸው መሆኑን የጠቆሙት የዓይን እማኞች ሹፌሩን ጨምሮ ሌላ አንድ የጥበቃ ፖሊስም አብሮ መሞቱ ታውቆዋል::

እስረኞችን ህገ ወጥ በሆነ መልኩ በሌሊት አሳፍረው እያጉዋጉዋዙ ከመውሰዳቸውም በተጨማሪ እስረኞቹ ከአደጋው ያልተረፉት እጃቸው በካቴና በመታሰሩ እራሳቸውን ለማዳን እንደተቸገሩና በቃላት ሊገለጽ የማይችል ዘግናኝ አደጋ ሊደርስባቸው እንደቻለ የአይን እማኞቹ አስረድተዋል::

አህያ ተገጨ እያሉ እያናፈሱ የሚውሉት የወያኔ አፈ ሊቅ የሆኑት ሚዲያዎች በግፍ እና በግዳጅ ታስረው በሚሰቃዩት ዜጎች ላይ ይህን የመሰለ ዘግናኝ አደጋ ሲደርስ እንደ ተራ

እና አልባሌ ነገር ዝም ማለታቸው በእጅጉ የሚያሳዝን ከመሆኑም በላይ ገመናችን ይወጣል በሚል የወያኔ ቡድን ጉዳዩን በምስጢር መያዙም ታውቆዋል።

አደጋው ከደረሰበት ማግስት ሐምሌ 12 ቀን 2002 ዓ.ም ጀምሮ የእስረኛ ቤተሰቦች ዝዋይ ያሉትን እንዳያዩ የተከለከሉ መሆኑን የጠቆሙት ውስጥ አዋቂ ምንጮች እስከዛሬ ድረስ ማን እንደሞት ቤተሰቦቻቸው ባለማወቃቸው እጅግ ከፍተኛ ሀዘን ውስጥ ወድቀው እንደሚገኙም ጨምረው ገልፀዋል።

የሙዋች ፖሊሶች አስከሬን አንደኛው አዲስ አበባ ሌላኛው መቀሌ ተጉዋጉዞ ስርዓተ ቀብራቸው እንዲፈጸም ሲደረግ የወያኔ አረመኔ ቡድን በግፍ ያሰራቸው እና በአደጋው የሞቱት እስረኞች አስከሬንን ቤተሰቦቻቸው ሳያውቁና ሳይሰሙ እንደ እንስሳ አዲስ አበባ አምጥቶ በማዘጋጃ ቤት ሰራተኞች በድብቅ እንዲቀበሩ ማድረጉንም ምንጮቹ ጨምረው አጋልጠዋል።

በየጊዜው እያፈሰ ለእስር የሚዳርጋቸው ዜጎች ቁጥር በየእለቱ እየጨመረ በመምጣቱ በመላ ሀገሪቱ የእስር ቤት ግንባታው እየተስፋፋ ከመምጣቱም በተጨማሪ እዚህ ግባ በማባይልና ምንም ማስረጃ በሌለው ክስ እየወነጀለ ለእስር የሚዳርጋቸው ዜጎች በመብዛታቸው የተለያዩ እስር ቤቶች እንዲታጎሩ ከመደረጋቸውም በላይ ለተለያዩ በሽታዎች ተጋልጠው እንደሚገኙ ይሄው የደረሰን ጥቆማ አብራርቶዋል።

ህክምናውን ለማግኘት አቅም ያላቸው እስረኞች በገንዘባቸው እንታከም እያሉ ጥያቄ ቢያቀርቡም አድማጭ እና ሰሚ አጥተው በከፋ ህመም እየተሰቃዩ ሲሆን ገሚሶቹም በዚያው እስር ቤት እየሞቱ እንደሚገኙ ታውቆዋል።

ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ብዙ ጊዜ በተለያዩ ህመሞች ተጠቅታ በቂ ህክምና ወደ ምታገኝበት ቦታ እንድትወሰድ ወላጅ እናትዋ እና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ተደጋጋሚ ግዜ ጥያቄ ቢያቀርቡም ጥያቄያቸው ተቀባይነት አጥቶ ውድቅ የተደረገ ከመሆኑም በተጨማሪ ከውጭ ተገዝቶላት የሚገቡ በሀኪም የተረጋገጡ መድሀኒቶች እንዳይሰጥዋት በመደረጉ በአሁኑ ሰዓት ህመምዋ እየባሰባት እንደሚገኝ ወላጅ እናትዋ ድረሱላት ሲሉ ገልጸዋል።

ለክብራቸው እንጂ ለህዝቡ ነጻነት የማይጥሩ.....ለዝናቸው እንጂ ለህዝቡ ልዕልና የማይሰሩ.....ገንዘባቸውን ማከማቸት እንጂ ለህዝቡ ኑሮ ደንታ የሌላቸው የተቃዋሚ ፓርቲ መሪ ነን የሚሉት እድሜ ጠገብ ፖለቲከኞች ወጣቱዋን ፖለቲከኛ እስር ቤት አስገብተው ከወያኔ ጋር አንዴ ሽራተን ሌላ ጊዜ ግዮን እያሉ ከመለስ ዜናዊ ጀምሮ እስከ ግልገል ሹማምንት በምስጢር እና በይፋ ሲሞዳሞዱ ቢከርሙም ውጤቱ እንዳሰቡት ሳይሆን ቀርቶ የጠበቁት እና የፈለጉት ዝናና ክብር ያጡት መሆኑን የግንቦቱ ምርጫ ያረጋገጠ ነው ያሉት አንድ ስማቸው እንዲገለፅ ያልፈለጉ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፖለቲካል ሳይንስ መምህር አሁንም በእስር ላይ ሆና ታላቅ ሰው መሆንዋን ያስመሰከረች ቆራጥ ኢትዮጵያዊ መሆንዋን ሁሉም ዜጋ ያውቀዋል ሲሉ በንዴት አስተያየት ሰጥተዋል።

በአሁኑ ሰዓት ዜጎች እንደ እንስሳ ከየቤቱ እየታፈሱ ለእስር ሲዳረጉ አንዳችም ተቃውሞ የማያሰሙትና ይባስ ብለው እርስ በርስ እንደተናካሽ ውሻ እየተባሉ ያሉት የተቃዋሚ መሪ ነን የሚሉት እነዚሁ እድሜ ጠገብ ግለሰቦች ለወያኔ ስልጣን መራዘም አንዱና ዋነኛ መሆናቸው ሊታወቅ ይገባል ሲሉም እኚሁ ምሁር አጽንኦት ሰጥተው ሲገልጹ ተደምጠዋል።

በሌላ ዜና ግራ የገባው ወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ሰሞኑን አሉ የተባሉ የሀገሪቱን ከፍተኛ ባለ ሀብቶች በምስጢር ቤተ መንግስት አስጠርቶ ጠንከር ያለ ማስፈራሪያ መስጠቱ ተጋለጠ።

ለተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ድጋፍ ያደርጋሉ በሚል ከፍተኛ ወከባና እንግልት ሲደርስባቸው የነበሩትን በለሀብቶች ዘንድሮም እንደ ሌላው ጊዜ ሁሉ ለማስደንገጥ አራት ኪሎ ቤተ መንግስት ውስጥ በሚገኘው የመሰብሰቢያ አዳራሽ ውስጥ ሰብስቦ ማስፈራራቱ ታውቆዋል።

መለስ ዜናዊ ባለሀብቶቹን ጠርቶ ባነጋገረበት ወቅት «.....ለውጭ ሀገር ኤምባሲዎች የምታሾከሹኩ እንዳላችሁ ደርሰንበታል .......በምስጢር አሁንም ለተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች ድጎማ የምትሰጡ አላችሁ..... አንዳንዶቻችሁ የኢህአዴግን ንግድ ድርጅቶች ለመጣል እያሴራችሁ መሆኑን ታውቆዋል.......»የሚሉና ሌሎች ጸያፍ ስድቦችን ጭምር መናገሩን የጠቆሙት ተሰብሳቢዎቹ የገንዘብ ችግር ስላጋጠመው አስደንግጦ ለመውሰድ ያሰበው ስልት ሳይሆን አይቀርም ሲሉም ያላቸውን ግምት ገልጸዋል።

«....ከእኛ ሀሳብ እና እቅድ ውጭ ብትንቀሳቀሱ የያዛችሁት ሀብት ዜሮ ሊወጣ ይችላል .....አስፈላጊ ከሆነ በ10 ደቂቃ ሁሉንም ሀብት ልታጡ ትችላላችሁ.... ደረታችሁን የምትነፉበት ገንዘብ እኛ በፈጠርነው ዲሞክራሲ መሆኑን ማወቅ አለባችሁ.......የተቃዋሚ መሪዎችም ሆነ አምባሳደሮች በእኛ ላይ የሚፈጥሩት አንዳችም ጫና የለም......» ሲልም ዛቻ እና ማስፈራሪያ ሲሰነዝር እንደዋለ ታውቆዋል።

ባለፈው ወር ሰኔ መገባደጃ ላይ ድንገት በሀገሪቱ ውስጥ አሉ የተባሉና በተለይ ከተቃዋሚ መሪዎች ጋር ይሞዳሞዳሉ የአምባሳደሮችን ትኩረት ይስባሉ በተባሉት ባለሀብቶች እና ቀድሞ ዲያስፖራ የነበሩት ላይ ይሄን መሰሉ ጫና ሊፈጠር የቻለው የወያኔ ቡድን መሪዎች የተሳሳተ ግንዛቤ በመያዛቸው ነው ያሉት ተሰብሳቢዎቹ እንዲህ ያለ አጉራ ዘለል እና ማን አለብኝነት ለማንም አልበጀ ሲሉ በምሬት ሲገልጹ ተደምጠዋል።

እስከ አሁን ድረስ በዓለም ላይ ያየናቸው አምባገነን መሪዎች ጡንቻቸውን የሚያፈረጥሙት አሜሪካ በምታደርግላቸው ድጋፍ መሆኑን የጠቆሙት እነኚሁ ባለሀብቶች ሁኔታዎች ሲቀየሩ ወዳጆቸዋ የነበሩትን አንቅራ እንደምትወረውር እነ ቻርልስ ቴለር ...... ሳዳም ሁሴን እና ሌሎችን መመልከት በቂ ምስክር ነው ሲሉም በመለስ ፊር የሳተ ንግግር እንባ እየተናነቃቸው ሲናገሩ ተደምጠዋል።

ይብዛም ይነስ መለስን ጨምሮ አሉ ከተባሉት የወያኔ ቁንጮ ባለስልጣናት በላይ የተሻለ ትምህርት እና ችሎታ ያለን ሰዎች የተሰባሰብንበት የንግዱ ማህበረሰብን እንደ ተራ እና አልባሌ ሰዎች በመቁጠር አላስፈላጊ ትችት እና ስድብ ማሳቀፉ እጅግ የሚያሳፍር እና ለዜጎች ያለውን ክብር ያወረደ መሆኑን የተረዳንበት ነው ሲሉ በስብሰባው ላይ የነበሩት ባለሀብቶች በቁጭት እና በእልህ ሲገልጹ ተደምጠዋል።

የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ዛሬ በተለያዩ አቅጣጫዎች በነጋዴው ህብረተሰብ ላይ በተለይ ውጭ ሀገር ኖረው በመጡ ኢንቨስተር ኢትዮጵያውያኖች ላይ ወከባና ጫና እየፈጠረ ያለው ቀስ በቀስ

በተቃዋሚ ፓርቲዎች ጀርባ ተከልለው በመግባት ስልጣኑን ያስጥሉኛል የሚል ስጋት በማሳደሩ ነው ሲሉ አንድ ስማቸው እንዲጠቀስ ያልፈለጉ ባለሀብት አጽንኦት ሰጥተው ገልፀዋል፡፡

በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የነጋዴዎች ወይም ኢንቨስተሮች አይን ቀለም አላመረኝም በሚል ሰበብ እስከ ዛሬ ድረስ አንዳችም ትንፍሽ ሳይል የቀረበትን ነገሮች ከ18 ዓመታት በሁዋላ እንደ አዲስ እተመለከተ ሰበብ እየፈጠረ ክስ መስርቶ ወደ ዘብጥያ እያወረዳቸው መሆኑ እጅግ አሳዛኝ ከመሆኑም ባሻገር ለሀገር የማይጠቅም የበቀል እርምጃ መሆኑን የደረሰን ዘገባ ያስረዳል፡፡

ሰሞኑን በአራጣ አበዳሪነታቸው የሚታወቁት አቶ አየለ ደበላ የተባሉት ባለሀብት (በቅጽል ስማቸው አይ.ኤም.ኤፍ) የወያኔ ቡድን የውጭ ምንዛሪ ባጣበት ወቅት ሳይቀር ለነጋዴው ህብረተሰብ የጀርባ አጥንት ሆነው ሲያገለግሉ የነበሩ ቢሆንም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ክስ መስርቶባቸው የ22 ዓመት ጽኑ እስራት እና 308 ሺ.ህ ብር ቅጣት ጥሎ እጅግ ዘመናዊ ህንፃዎቻቸውን..... ሙሉ ንብረቶቻቸውን...... በባንክ ውስጥ የነበራቸው በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር ብር...... በቤታቸው ውስጥ የተገኘ መጠኑ ያልታወቀ በሚሊዮን የሚቆጠር ዶላር እንደተወረሰባቸው ታውቆዋል፡፡

ወያኔ ህጉን ለማስከበር እና የሀገርን ጥቅም ለማስጠበቅ ብሎ የወሰደው እርምጃ አይደለም ያሉት ስማቸው እንዲገለጽ ያልፈለጉ የአንድ ኩባንያ ባለቤት ከዚህ ቀደም ይሄን ስራ ግለሰቡ እንደሚሰሩ እየታወቀ አልፎ ተርፎ ታላላቅ የተባሉ የወያኔ ባለስልጣናት ጭምር ብድር ከእኚሁ ግለሰብ እየወሰዱ እንደነበር አስታውሰው ባለስልጣናቱ የተበደሩትን ገንዘብ ላለመመለስ በማሰብ ለሀገር እና ለወገን በማይጠቅም መልኩ በበቀል ላይ በመመስረት ግለሰቡን በህይወት እንዳይኖሩ የሚያደርግ እርምጃ መወሰዱ በእጅጉ ያሳዝናል ያሳፍራልም ሲሉ ገልፀዋል፡፡

የበቀል ውሳኔ መሆኑን የሚያስታውቀው ግለሰቡ በባንክ የነበራቸው ገንዘብ.....በቢሮዎቻቸው እና መኖሪያቸው የተገኘው የውጭ ሀገር በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ......የመኖሪያ ልዩ ቪላዎቻቸው.........በአራት ኪሎ ከብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት ፊት ለፊት የሚገኘውን ያልተጠናቀቀ ዘመናዊ ህንፃ ከመውረሳቸውም በላይ ለሰዎች ያበደሩትን ገንዘብ እንዳይጠይቁ የሚደነግግ ውሳኔ እንደተጣለባቸውና ባዶ እጃቸውን መሆናቸው እየታወቀ 308 ሺ.ህ ብር ቅጣት እና 22 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጡ መወሰኑ የበቀል እርምጃ መሆኑ ያስታውቃል ሲል የደረሰን ዘገባ አብራቶዋል፡፡

በእኚህ ግለሰብ ላይ የተወሰደው እርምጃና በሌሎች ባለሀብቶች ላይ በሻት ማጭበርበር ስም በወረንጦ እየተለቀሙ ወደ ዘብጥያ የሚወርዱት ዜጎች ከቀን ወደ ቀን ቁጥራቸው እያሻቀበ መምጣቱ አስደንጋጭ ከመሆኑም በላይ ቀስ በቀስ የወያኔ አባል ነጋዴዎች ብቻ ሙሉ ለሙሉ በሀገሪቱ ውስጥ ያለውን ንግድ ለመቆጣጠር ሆን ተብሎ የተቀነባበረ ስልት መሆኑን ሁሉም ዜጋ ሊያውቀው እንደሚገባም እየተነገረ ይገኛል፡፡